19ኛ አመት ቁጥር 4

19th Year No 4

ባህር ዳር መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም

Bahir Dar 4th, April, 2014

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ-ሕግ

ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 12.00 Price	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	Contents
ደንብ ቁጥር 121/2006 ዓ.ም	Regulation No.121/2014
በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	The Amhara National Regional State Charities and Societies Registration and Administration Determination Reulation Amendment, Council of Regional Government Regulation

ደንብ ቁጥር 121/2006ዓ.ም	REGULATION No.121/2014
በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገብና አስተዳደር መወሰኛ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	A REGULATION ISSUED BY THE COUNCIL OF THE REGIONAL GOVERNMENT TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE REGISTRATION AND ADMINISTRATION OF THE CHARITIES AND SOCIETIES DETERMINATION REGULATION IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

በክልሉ ውስጥ በበጎ አደራጎት ስራ ለመሰማራት ወይም የአባሎቻቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለማስከበር ይቻላቸው ዘንድ በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ወይም በማህበርነት ለመመዝገብና እንቅስቃሴ ለማድረግ ከሚፈልጉት መካከል ተፈላጊውን የምዝገባ አገልግሎት ክፍያ የመክፈል አቅም የሌላቸው አንዳንድ ማህበራት ወይም ተቋማት ከአገልግሎት ክፍያ ነፃ ሆነው እንዲመዘገቡ የሚያስችል አሰራር መዘርጋትና ለዚሁ ያመች ዘንድ በስራ ላይ ያለውን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ደንብ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

Whereas, it is found necessary to put in place a working procedure which would, from among those charities or societies that are registered as such and thereby desire to engage in charitable activities or to enforce the rights and benefits of their respective members throughout the Region, enable some societies or institutions which cannot otherwise afford to pay the required registration service charge to be duly registered with the exemption of such charges and, to that end, amend the existing Charities and Societies Registration and Administration Regulation in force;

የአማራ ክልል መስተዳደር ምክር ቤት በተሸሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና የክልሉን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ለመመዝገብና ለማስተዳደር በወጣው አዋጅ ቁጥር 194/2004 ዓ.ም. አንቀፅ /107/ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

Now, THEREFORE, the Council of the Amhara Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub-Art. 7 of the Revised National Regional Constitution and Art. 107 Sub. Art. 1 of the Regional Proclamation No.194/2012 enacted to provide for the Determination of the Registration and Administration of Charities and Societies, hereby issues this regulation:

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 121/2006 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

1. Short Title

This regulating may be cited as "The Charities and Societies Registration and Administration Determination Regulation Amendment, Council of Regional Government Regulation No. 121/2014."

2. ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ምዝገባና አስተዳደር መወሰኛ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 117/2005 ዓ.ም እንደሚከተለዉ በዚህ ደንብ ተሻሽሏል፡፡

በደንቡ አንቀጽ 65 ስር የሰፈረው ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 ከሆነ በኋላ ከዚህ በታች የተመለከተው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጨማሪነት ገብቷል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ ቢኖርም ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ጥያቄ በዚህ ደንብ መሠረት ለምዝገባ ወይም ለሌሎች አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን በከፊል ወይም በሙሉ ቀሪ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ደንቡን ለማስፈጸም በቢሮው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

3. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር
መጋቢት 26 ቀን 2006 ዓ.ም.
ገዱ አንዳርጋቸዉ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር

2. Amendment

The Amhara National Regional State Charities and Societies Registration and Administration Determination, Council of Regional Government Regulation No. 117/2013 is hereby amended by this Reulation as follows:

The Provision laid down under Art.65 of the Regulation is numbered Sub-Art.1 and the following new Sub-Art.2 is additionally inserted therewith:

2. Notwithstanding the general provision laid down under Sub-Art. 1 of this Article hereof, the Bureau may, where it finds it necessary, partially or wholly exempt the charges required for the registration or other services pursuant to this Regulation upon the request of any charity or society. Particulars shall be determined in a directive which the Bureau may issue to implement the Regulation.

3. Effective Date

This Regulation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

Done at BahirDar
This 4th day of April, 2014
Gedu Andargachew
Head of Government of the Amhara National Regional State